በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኤፕሪል 1-30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ

## ግምገማ እንዲሁም

## ከሜይ 1-31/2024

## የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሜይ 2024

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ - 1 -

ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 3 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 4 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ..... - 4 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ..... - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 6 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ ........ - 7 -

ካርታ 7፡ እ.ኤ.አ ከሜይ 1-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠንና ስርጭት ........ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -

እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 9 -




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በአፕሪል የመጀመሪያው አስር ቀናት በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራብ እንዲሁም በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበረው ጠንካራ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በሁለተኛዉ አስር ቀናት ደግሞ በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የዝናቡ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በስጭርት የመቀነስ አዝመሚያ የታየበት ቢሆንም በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው እና ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በሶስተኛዉ አስር ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፣ በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን ሲገባ የነበረዉ እርጥበት አዘል አየር ይበልጥ በመጠናከሩ ምክንያት በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናት በደቡብ፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ እንዲሁም በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

በአጠቃላይ በኤፕሪል ወር በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት ብዙ የገሪቱ አከባቢዎችን ያዳረሰ ሲሆን፤ በበርካታ አከባቢዎች ላይም ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል፤ በአዲስ አበባ ቦሌ 34.0፤ በጅማ 33.8፤ በመተሃራ 36.0፤ በነገሌ 40.0 እና 36.0፤ በአቦምሳ 47.4፤ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 53.1 እና 81.4፤ በአዲግራት 34.3፤ በአማን 42.3 እና 35.2፤ በአምቦ 37.2፤ በአይሻ 113.0፤ በአዋሽ አርባ 57.2፤ በአርባ ምንጭ 41.8 እና 42.7፤ በአለም ተፈሪ 44.2፤ በአልጌ 45.0፤ በብላቴ 39.7፤ በቦሬ 36.0 እና 30.4፤ በቡሬ 55.0፤ በቡሌ ሆራ 36.3፣ 42.9 እና 73.8፤ በጨፋ 36.4፤ በዳሊፋጊ 33.7፣ 35.3፤ በደብረ ወርቅ 66.0፤ በዲላ 38.4 እና 30.5፤ በዶሎመና 30.2፤ በዱብቲ 37.5፤ በእንዋሪ 36.4፤ በጎዴ 30.5፤ በጊኒር 53.0፤ በሀዋሳ 32.3፤ በሆሳዕና 60.6፣ 46.5 እና 50.0፤ በእምድብር 36.1፣ 34.2 እና 43.1፤ በጅግጅጋ 61.7፤ በኮምቦልቻ



ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

52.3፤ በኮንሶ 58.4፣ 47.6 እና 32.5፤ በሊሙገነት 56.8 እና 35.5፤ በማጀቴ 61.6 እና 33.0፤ በማጂ 32.2፣ 37.0፣ 71.5 እና 42.7፤ በማሻ 30.6፤ በሞያሌ 84.0፣ 45.2፣ 49.5 እና 76.0፤ በሚሌ 54.0፤ በንፋስ መዉጫ 44.7፤ በኑራኤራ 34፣ 45.5 እና 34.1፤ በነጆ 31.2፤ በሳዉላ 52.4 እና 37.9፤ በሰመራ 30.0፤ በሲርንቃ 30.4 እና 39.0፤ በተርጫ 31.9፤ በወረኢሉ 43.0፤ በያቤሎ 40.4፤ በቁሉቢ 43.8፣ 38.6 እና 36.8፤ በደንገጎ 31.4፤ በላንጌ 32.6 እና 32.0፤ በጨለንቆ 48.0፣ 30.0፣ 42.4 እና 55.8፤ በፌድስ 40.0፤ በአዋሬ 40.0 እና 31.0፤ በሻላቦ 39.5፣ 61.0፣ 114.5 እና 47.5፤ በዶሎ 58.2፤ በጉብይሬ 49.8፤ በካራሚሌ 53.8፣ 33.9 እና 38.5፤ ኮምቦልቻ (ምስራቅ ሀረርጌ) 48.2 እንዲሁም በሀረዋ 34.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

በኤፕሪል ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከኦሮሚያ ክልል ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቀለም ወለጋ እና ጅማ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል ሲቲ፣ ፋፋን፣ ጀረር፣ ዶሎ፣ ኤረር፣ ቆራሄ፣ ሸበሌ፣ ኖጎበ፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ ዞን፤ ሁሉም የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል እና የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ የኦሮሞ ልዩ ዞን፣ ሰሜን ሸዋ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ሀዉሲ፣ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ሀረሪና ድሬ ዳዋ ላይ 61-350 የሚደርስ ዝናብ ከ13-30 ቀናት ያህል ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ክልል ሰሜን፣ ማዕከላዊ፣ ደቡብ እና ምዕራብ ጎንደር፣ አዊ ዞን፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጃም፤ ከትግራይ ክልል ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምስራቅ ምዕራብ እና ማዕከለዊ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከል፣ አሶሳ፣ ካማሺ እና የማኦኮሞ ልዩ ዞን፤ ከጋምቤላ ክልል ኑዌር፣ አኝዋክ እና የኢታንግ ልዩ ዞን፤ ከአፋር ክልል ቂልበቲ እና ፈንቲ ዞኖች ላይ ከ4-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-12 ቀናት ያህል ነበራቸው (ካርታ 1 እና 2) ፡፡


በኤፕሪል ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምስራቅ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ቄለም ወለጋ እና ምዕራብ ወለጋ ዞኖች፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣ ዳዉሮ፤ከፋ፣ ሸካ ኮንታ እና ደቡብ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ኦሞ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል አማሮ፣ ቡርጂ፣ ደራሼ፣ ኮንሶ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ወላይታ፣ ጌደኦ፣ ኣሪ እና አማሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ ሀላባ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ስልጤ፣ ጠምባሮ እና የየም ልዩ ዞን፤ ከሱማሌ ክልል ዶሎ፣ ጀርረ፣ ፋፋን፣ አፍዴር፣ ኤረር፣ ሊበን፣ ዳዋ እና ሲቲ ዞኖች፤ ከፋር ክልል ቂልበቲ፣ ፋንቲ፣ ሀሪ እና ጋቢ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ዋህግምራ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፣ ሀረሪ እና ድሬ ዳዋ ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡


በሌላ በኩል በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ36-43.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ምስል1) ።





ምስል 1 የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ
የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ
ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ካርታ 4 ኢ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ
የነበረዉ የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ወር በተለይም የበልግ አብቃይና ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት የበልግ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴን ለማከናወን፣ ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለጓሮ አትክልቶችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡

በተጨማሪም የተገኘው እርጥበት አስቀድመው ለሚዘሩ የመኸር ወቅት ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ምቹ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡

በሌላ በኩል በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በረባዳማ እና የአፈር ጸባያቸው ውሃን በማያስርጉ ማሳዎች እንዲሁም በወንዝ ዳርቻ አካባቢዎች በሚገኙ ማሳዎች ላይ የወሃ በሰብሎች ላይ መተኛት እና በደለል የመሞላት እንዲሁም በጎርፍ የመጠረግ ሁኔታዎች ነበሩ (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኤፕሪል ወር በገናሌ ዳዋ፣ በላይኛው አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው። በተጨማሪም በአብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አባይ እንዲሁም በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህም ሁኔታ የገጸ ምድርንም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ሀብትን በማጎልበት ወደ ተለያዩ የውሃ መያዣዎች እና ማጠራቀሚያዎች የሚገባውን የውሃ ሀብት ከመጨመር አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ የነበረው ቢሆንም፤ በአንዳንድ ተዳፋታማ እና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶችና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የጎርፍ ክስተቶችም ነበሩ። በሌላ በኩል በአብዛኛው ተከዜ እና የታችኛውና የመካከለኛው አባይ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል (ካርታ 6)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ


በመደበኛ ሁኔታ በሜይ ወር ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ከበልግ አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ በመሄድ ከክረምት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች መጠናከር ጋር ተያይዞ ዝናቡ ወደ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይስፋፋል፡፡

በመጪው ወር ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኞዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚጠናከሩና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀደሙት ሶስት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢ ላይ እንደሚኖርና በአንዳንድ ሥፍራዎችም ላይ ከባድ ዝናብ የሚዘወተርና አልፎ አልፎ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል እንደሚችል ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በሚቀጥለዉ ወር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲና ምዕራብ አርሲ፣ ባሌና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂና ምዕራብ ጉጂ፤ ቦረና፤ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ እንዲሁም ሐረሪ እና ድሬዳዋ፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ ዞኖች፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፣ የሰሜን ሸዋና የኦሮሚያ ልዩ ዞን፤ የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የደቡብ፣ የደቡብ ምስራቅ፣ የምስራቅ ትግራይ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሱማሌ ክልል ዞኖች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚያዳርስ የተስፋፋ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7በተለይም በሰሜን ምስራቅ፤ ስምጥ ሸለቆ፤ ምስራቅ፣ ደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ የሚኖረው ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ የማስከትል አቅም ሊኖረው ስለሚችል ማህበረሰቡና የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 7፡ እ.ኤ.አ ከሜይ 1-31፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠንና ስርጭት

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው ወር የሚጠበቀው እርጥበት የበልግም ሆነ በከፊል የመኸር ወቅት የግብርና ተግባራትን ለማከናወን የጎላ ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን ቀደም ብለው ለተዘሩና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ከሜይ ወር ጀምረው ለሚዘሩ የመኸር ሰብሎች፣ በከተማ ግብርና ለሚለሙ የጓሮ አትክልቶች እንዲሁም ለተለያዩ እፅዋቶች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪ የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ለከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማረጋገጥ አንጻር የጎላ ሚና ስለሚኖረው የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ የግብርና ግብዓቶችን ከወዲሁ በማዘጋጀት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል በተለይም በመደበኛ ሁኔታ የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ ያልሆኑ የአርብቶ አደር እና የከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች በቀሪ የበልግ ቀናት የሚገኘውን የዝናብ ውሃም ሆነ የእንስሳት መኖን በበቂ ሁኔታ በማሰባሰብ እና በተገቢው ቦታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

በማከማቸት ዘላቂ የእንስሳት ልማትና ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችል ዝግጅት እንዲያደርጉ በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ይመከራሉ።

በወሩ የሚጠበቀው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በአንዳንድ የአፈር ፀባያቸው ውሃ በማያሰርጉና ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብል ማሳዎች ላይ መተኛትን ሊያስከትል ስለሚችል ይህንን ለመከላከል የሚያስችል የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራትና እንዲሁም ተዳፋታማ እና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ማሳዎች ላይ ደግሞ ሰብሎች በጎርፍ ተጠርገው እንዳይሄዱ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በማዘጋጀት የቅድመ ጥንቃቄ ስራ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል የሚኖረው ምቹ የአየር ሁኔታ ለበረሃ አንበጣ መራባትና መሰራጨት ምቹ ሊሆን ስለሚችል የሚመለከታቸው አካለት አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከሜይ 1 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በዉ.ሀዉ. ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው የሜይ ወር በኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ ስምጥሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ አባይ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ኦጋዴን እና የላይኛው እና መካከለኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ የገፀ ምድር እና የከረሰ ምድር ውሃ ሀብትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡

በአንጻሩ ግን በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ የሚጠበቀው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ በንብረትና በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል አደጋን ለመቀነስ ብሎም ለማሰቀረት የሚያስችሉ መደበኛ የውሃ መፋሰሻዎችን የማጽዳት፣ የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን የማዘጋጀት እና ለጎርፍ ተጋላጭ የሆኑ የወንዝ ዳርቻዎችን የመገደብ ተግባራትን አስቀድሞ ማከናወን ያስፈልጋል።



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nma1@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et